# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ሀብትን የታደገው የተቋሙ ንብረት አስተዳደር

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለአገር ውስጥ ፍጆታና ለሽያጭ የሚሆን ኃይል የማምረትና የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም እንደመሆኑ የኃይል ማመንጫና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን እንዲሁም ረዥም ርቀት የሚጓዙና ከ132 ኪ.ቮ በላይ የሚሸከሙ የማስተላለፊያ መስመሮችን ይገነባል። ተቋሙ ለግንባታ ሥራ የሚያገለግሉትን አብዛኞዎቹን ግብዓቶች የሚያገኘው ከዓለም አቀፍ ገበያዎች በመሆኑ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያወጣ የሚፈልጋቸውን ቁሳቁስ ያስገባል። እነዚህ ቁሶች በጥንቃቄ ተይዘው፣ ተገጥመውና ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገባቸው አገልግሎታቸውን በአግባቡ እንዲከውኑ ማድረግም የተቋሙ የዘወትር ተግባር ነው።

ተቋሙ በሥራ እና በጥገና ሂደት ተፈትሸው ዳግም ለተቋሙ ሥራ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተረፈ ምርቶችን ቆጥሮና ሰፍሮ በመከዘን በግልጽ ጨረታ እየሸጠ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ያደርጋል። በዛሬው ጽሑፋችንም ከዚህ ተግባር ጀርባ ስላለው የተቋሙ የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ያሰናዳነውን ጽሑፍ ልናስነብባችሁ ወድደናል። መልካም ንባብ!

አቶ ታደሰ ዳዲ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የንብረት አስተዳደርና እና ጥገና መምሪያ ዳይሬክተር ናቸው። እንደ እርሳቸው ገለጻ የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ በሥሩ ሦስት መምሪያዎችን አቅፏል። እነዚህም የንብረት አስተዳደር መምሪያ፣ የፋሲሊቲ፣ አርካይቭ እና ዶክመንቴሽን መምሪያ እንዲሁም የተሸከርካሪ ስምሪት እና አስተዳደር መምሪያ ናቸው።

የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ቀድሞም የነበረ አደረጃጀት ሲሆን የቀድሞው የኢትዮጵያ


አቶ ታደሰ ዳዲ

ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን በ2006 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚሉ ሁለት የተለያዩ ሚና ባላቸው ተቋማት ከተከፈለ በኋላ በአዲስ መልክ ተደራጅቷል። ተቋሙ ከፍተኛ ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅስ እንደመሆኑ ኢኮኖሚውን የተሸከሙ ንብረቶችን በአግባቡ ለማስተዳደር አስችሏል። ተቋሙ የሚገነባቸውና የሚያስተዳድራቸው አብዛኞዎቹ ታዳሽ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ናቸው። እነዚህም የውሃ፣ የንፋስ፣ የቆሻሻ፣ የጂኦተርማል (አሉቶ ላይ ገና በመገንባት ላይ ያለ) ናቸው። ከዚሁ ጎን ለጎን የማከፋፈያ ጣቢያዎችና እና ከፍተኛ ቮልት ተሸካሚ መስመሮችን እየገነባ ያስተዳድራል። ከነዚህም በላይ በርካታ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች እንዳሉት የተናገሩት ዳይሬክተሩ በአጠቃላይ ንብረቶቹን በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለተቋሙ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ሲባል የንብረት አስተዳደር ዘርፍ መቋቋሙን አስረድተዋል።

እንደንብረትና ጥገና መምሪያም ንብረትን በዘመነ ሁኔታ ማስተዳደር እየተቻለ መሆኑን ገልጸዋል። ለምሳሌ የእቃ ግምጃ ቤትን በካይዘን አሠራር መሠረት መምራት እየታቻለ ነው ብለዋል። ንብረትን በዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ውስጥ ማስገባትና ወቅታዊ የማድረግ አካሄድን ይከተላል። ለምሳሌ አዲስ የእቃ ግዢዎች ሲፈጸሙ፣ ለአገልግሎት ተብለው ካሉበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲተላለፉ፣ ወይም አግልግሎት ጨርሰው ሲወገዱ ንብረቶች እንዳሉበት ቁመና በትክክል እየተለዩ እንዲቀመጡና በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ይህ አሠራር ንብረቶችን ከብክነት ለማዳን እና በአግባቡ ለሚፈለው ዓላማ እንዲውሉ ለማድረግ አስችሏል።

ድርጅቱ ካሉት አንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ ተሸከርካሪዎች ውስጥ ከስድስት መቶ በላይ በሚሆኑት ላይ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ የአቅጣጫ ጠቋሚ መሥሪያ ሥርዓት (GPS) በመግጠም ሰዎች በተለይም ኃላፊዎች ስለተሸከርካሪው ሁለንተናዊ ሁኔታ እንዲከታተሉ ተችሏል። የተቋሙ የሥራ ቦታዎች በአመዛኙ ከከተሞች ስለሚርቁና ተሽከርካሪዎችም አብዛኛውን ጊዜ መስክ ስለሚሠማሩ አሠራሩ የተሽከርካሪዎቹን ደህንነትና አላስፈላጊ ጉዞዎችን በመቆጣጠር በተቋሙ ላይ የሚደርሰውን የነዳጅ፣ የጎማ፣ የጊዜ ብክነት ለመቆጣጠር አስችሏል።

ተቋሙ ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች በርካታ እቃዎች በውጭ ምንዛሪ ተገዝተው እንደሚገቡ የጠቆሙት ኃላፊው ለተቋሙ አገልግሎት የማይሰጡ እንደ ቁርጥራጭ ብረታብረት፣ አልሙኒየም፣ መዳብ ያሉት የፕሮጀክት ተረፈ ምርቶች እንዲወገዱ ለሥራ ክፍሉ ሪፖርት ይቀርባል። ሥራ ክፍሉም የቀረበለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ በንብረት አወጋገድ ሥርዓት መሠረት ግልጽ ጨረታ በማውጣት የንብረት ማስወገድ ሥራ ያከናውናል። ሥራ ክፍሉ በ2015 ዓ.ም ብቻ የተወገዱ ንብረቶችን በጨረታ በመሸጥ ተቋሙ ከ113 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንዲያገኝ አስችሏል።

በተጨማሪም ኢንሹራንስ የሚገባለትን እና የማይገባለትን ንብረት ለይቶ በማስቀመጥ ሊወጣ የነበረውን 54 ሚሊዮን ብር ማስቀረት ተችሏል። በተጨማሪም የኃይል ማመንጫና የማከፋፈያ ጣቢያዎችን እንዲሁም የመሥሪያ ቤቶቹን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማሠራት ቋሚ ንብረቱን የማስጠበቅ ሥራ ሠርቷል። ተቋሙ በአሁኑ ሰዓት በተለይም ለዋና መሥሪያ ቤት ኪራይ ይከፈል የነበረውን ከፍተኛ ገንዘብ አስቀርቶ በራሱ ቢሮ ውስጥ ሥራዎችን ማከናወን ጀምሯል። በተጨማሪም ለ145 ኃይል ማከፋፈያና ለዘጠኝ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሠርቶ ግብር እንዲከፈልባቸው ተደርጓል። ይዞታ በማረጋገጥና በካሣ ክፍያ ወቅት የሚያጋጥሙት ችግሮች ፈታኝ እንደነበሩ ያስታወሱት አቶ ታደሰ ካሣ ከተከፈለ በኋላ አልተከፈለንም o ወይም አንሶናል በሚሉ ምክንያቶች ሥራዎች ሲስተጓጎሉ እንደነበር እና ካርታ ሲጠየቅም የአካባቢ መስተዳደሮች አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት ችግር እንደነበረባቸው አስረድተዋል።

ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል የአንድ ሀገር እድገት ሊረጋገጥ እንደማይችል የተናገሩት አቶ ታደሰ ተቋሙ በገነባቸው ግዙፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈጸም ስርቆት ተቋሙን ለከፍተኛ ወጪ ከመዳረጉም በላይ የተቋሙን ሕልውና እየተፈታተነው ይገኛል። ስለሆነም ኅብረተሰቡ በተቋሙ ንብረቶች ላይ የሚፈጸመው ስርቆት የሚጎዳው "እኔንም ሀገሬንም ነው" የሚል አስተሳሰብን ሊላበስ ይገባል። በተቋሙ ላይ የሚደርስ ኪሳራ ተቋማዊ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ ጭምር ነው። በመሆኑም የተቋሙን ንብረቶች እንደራስ ንብረት መጠበቅና ስርቆት የሚፈጽሙ አካላትን ተከታትሎ ለሕግ ማቅረብ የሁሉም ዜጎች ኃላፊነት እንደሆነ አቶ ታደሰ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል